# ስለምግብ ካርድ ኘሮግራም
# ማወቅ የሚገባዎ 10 እውነታዎች

**እውነታ** ፦ የምግብ ካርድ ፕሮግራም የማህበራዊ ደህንነት ፕሮግራም አይደለም። አነስተኛ ገቢ ያላቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች የተመጣጠነ ምግብ ገዝተው መመገብ እንዲችሉ ታስቦ የታቀደ የአመጋገብ ዘዴ ድጋፍ ፕሮግራም ነው።

**እውነታ** ፦ የምግብ ካርድ ፕሮግራም የባለመብትነት ፕሮግራም ነው። በሌላ አባባል  የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን ያመለከተና የፕሮግራሙን መስፈርት ያሟላ ሁሉ የምግብ ካርድ ተጠቃሚ ይሆናል።

**እውነታ** ፦ የምግብ ካርድ ተጠቃሚ የሚሆኑት ብቁ የሆኑ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ናቸው። ይህም ማለት አረጋውያንና አካለ ስንኩላንን፣ ስራ ላይ የተሰማሩ የቤተሰብ አባላትን፣ የተወሰኑ ህጋዊ ኢሚግራንቶችንና ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ  የተወለዱ ልጆቻቸውን ይጨምራል።

**እውነታ** ፦ ግለሰቦች የምግብ ካርድ ተጠቃሚ ሆነውም ቤት ሊኖራቸው ወይም ሊገዙ ይችላሉ። ቤቱና ቤቱ ያለበት መሬት በምግብ ካርድ ፕሮግራሙ ውስጥ እንደ ገቢ ምንጭ አይቆጠሩም። የምግብ ካርድ ፕሮግራሙ ግለሰቦች ቤታቸውን በሌላ ስም እንዲያዛውሩ አይጠብቅባቸውም።

**እውነታ** ፦ በ 2000 ኢ.ም. ብቻቸውን የሚኖሩ አረጋውያን በአማካይ በወር $43 ዶላር የተቀበሉ ሲሆን ብቻቸውን የማይኖሩ አረጋውያን ደግሞ  በአማካይ በወር $118 ዶላር ተቀብለዋል።

**እውነታ** ፦ አንድ አዛውንት ወይም አካለ ስንኩል ወደ ምግብ ካርድ ቢሮ መሄድ የማይችሉ ከሆነ በስልክ ቃለ መጠይቁ እንዲደረግላቸው መጠየቅ ይችላሉ። ወይም ደግሞ ጎረቤታቸው፣ ዘመዳቸው፣ የህይማኖት መሪዎቻቸው፣ ወዘተ የሆኑ ሰዎች ተወክለው ሄደው ቃለ መጠይቁን በነርሱ ስም ሊያካሄዱላቸው ይችላሉ። የተጨማሪ የደህንነት ገቢ (Supplemental Security Income - SSI) ተጠቃሚ የሆኑ ወይም ለመጠቀም ያመለከቱ ሰዎች ለምግብ ካርድ ተጠቃሚነት እማህበራዊ ደህንነት ቢሮ ሄደው ሊያመለክቱ ይችላሉ።

**እውነታ** ፦ የኢንሹራንስ ኩባንያ ወይም የቤተሰቡ አባል ያልሆነ ሰው እስካልሸፈናቸው ድረስ በወር ከ $35 ዶላር የሚበልጡ የህክምና ወጪዎች ከጠቅላላው የቤተሰቡ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይሆናል። ከ $35 ዶላር በላይ ያለው ሊቀነስ ይችላል።

**እውነታ** ፤ አዛውንት ቤተሰቦች ወይም አንድ አዛውንት ላለበት የምግብ ካርድ ተጠቃሚ ቤተሰብ ሊኖራቸው የሚገባው የገንዘብ መጠን እስከ $3000 ዶላር ነው። ሌሎች የምግብ ካርድ ተጠቃሚ ቤተሰቦች ሊኖራቸው የሚገባው የገንዘብ መጠን ግን እስከ $2000 ዶላር ነው።

**እውነታ** ፤ ቤተሰቦች የምግብ ካርድ ተጠቃሚ ሆነውም ምግብ–በጎማ፣ ልዩ ተጨማሪ የአመጋገብ ዘዴ ፕሮግራም ለሴቶች፣ ለህጻናትና ለልጆች (Meals-on-Wheels, Special Supplemental Nutrition Program for Women, Infants and Children-WIC) ጥቅሞችን፣ እና እንደ የትምህርት ቤት ምሳ ፕሮግራም (School Lunch Program) ያሉትን የልጆች ምግብ–ነክ ጥቅሞችን ሊቀበሉ ይችላሉ።

**እውነታ** ፤ የምግብ ካርድ ፕሮግራም ተጠቃሚ መሆን ህጋዊ ኢሚግራንቶች ያሉበትን ቤተሰብ «የመንግሥት ሸክም» አያደርገውም።

**የምግብ ካርዶች አሜሪካን ያጎለብቷታል**

የዩናይትድ ስቴትስ የግብርና ሚኒስቴር (United States Agriculture Department - USDA) ለሁሉ እኩል እድል ሰጪ እና ቀጣሪ ነው።